በልደታ ክፍል ከተማ የተስፋ ኮከብ ጉድኝት ማዕከል የ **2015** ዓ.ም የመጀመርያ መንፈቀ ዓመት የ **6**ኛ ክፍል የሒሳብ ሞዴል ፈተና

የተሰጠው ሰዓት ***1*** ሰዓት

ስም ______________________ ክፍል _______ቁጥር________________

I. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛው መልስ የያዘው ሆሄ በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ መልሱ።

________1. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ውስጥ ኢ-ተጋማሽ ሙሉ ቁጥር የቱ ነው?

ሀ. 88,768 ለ. 77,990 ሐ. 88,745 መ. 11,346

________2. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ውስጥ ለ3እና ለ9 ተካፋይ የሚሆነው ምረጡ።

ሀ. 27,891 ለ. 30028 ሐ. 34,894 መ. 99,073

________3. $824 \div 4 =$ መ ከሆነ የ "መ" ዋጋ ስንት ነው?

ሀ. 26 ለ. 206 ሐ. 406 መ. 403

________4. 7.34 ወደ መቶኛ ሲለወጥ የትኛው ይሆናል?

ሀ. 73.4% ለ. 734% ሐ. 7340% መ. 6.734%

________5. ትክክለኛውን ዐረፍተ ነገር የሆነውን ምረጡ።

ሀ. የ 5 ተካፋይ የሆኑ ቁጥሮች ሁሉ የ 10 ተካፋይ ናቸው።

ለ. ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር አካፋይ ሊሆን የሚችል ሙሉ ቁጥር የለም።

ሐ. 1 ብቸኛ ሙሉ ቁጥር ነው።

መ. ለ 8 ተካፋይ የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች ለ 4 ተካፋይ ናቸው።

________6. ከሚከተሉት ቁጥሮች ውስጥ ተጋማሽ እና ብቸኛ የሆነውን ምረጡ

ሀ. 3 ለ. 19 ሐ. 2 መ. 9

________7. የተካፋይነት ደንብን በተመለከተ ትክክል የሆነውን ዐረፍተ ነገር ምረጡ።

ሀ. ዜሮ ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር አካፋይ ሊሆን ይችላል።

ለ. 1 ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር አካፋይ ነው።

ሐ. አንድ ሙሉ ቁጥር ለ 2 የሚካፈል ከሆነ ለ 4 ይካፈላል።

መ. አንድ ሙሉ ቁጥር ለ 5 የሚካፈል ከሆነ ለ 10 ይካፈላል

________8. መ፣ቀ እና በ መቁጠሪያ ቁጥሮች ቢሆኑ እና መ÷ ቀ ¿ በ ከሆነ፣ ትክክል ያልሆነው ዐረፍተ ነገር የትኛው ነው

ሀ. “መ” የ ቀ ተካፋይ ነው::   ሐ. “በ” የቀ ተካፋይ ነው::

ለ. “መ” የቀና መ ብዜት ነው::   መ. “ቀ” የመ አካፋይ ነው::

________9. 252 በብቸኛ ትንትን ሲገለፅ፡-

ሀ. $2^3 \times 3 x 5^2$ ሐ. $2^2 \times 3^2 \times 7$

ለ. $2^2 \times 3^2 \times 5 \times 7$ መ. $2^3 \times 3^2 \times 7^2$

________10. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክለኛውን ዐረፍተ ነገር ምረጡ።

ሀ. ተከታታይ የሆኑ ብቸኛ ሙሉ ቁጥር የሉም።

ለ. ትንሹ ተተንታኝ ሙሉ ቁጥር 8 ነው።

ሐ. ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ 1 እና ለራሱ ተካፋይ ነው።

መ. 1 ብቸኛም ተተንታኝም ቁጥር አይደለም

________11. አበበ አንዱ ብርትኳን አምጥቶ እኩል 11 ቦታ ከፋፈለው። ከክፍልፋዮቹ መካከል 5 ቱን ለደረራ

ቢሰጥ፣ የደረራ ድርሻ በክፍልፋይ ሲገለፅ፡-

ሀ. $\frac{11}{5}$❑   ለ. $\frac{5}{11}$❑   ሐ. $\frac{11}{5}$❑   መ. $\frac{11}{6}$❑

________12. ከሚከተሉት ጥንድ ቁጥሮች ውስጥ አንፃራዊ ብቸኛ ቁጥሮች የሆኑት የትኞቹ ናቸው?

ሀ.16እና100   ለ.25እና49   ሐ. 75እና120   መ. 77እና140

________13. $3^{\frac{1}{4}}$ ወደ መቶኛ ሲለወጥ፡-

ሀ. $\frac{31}{4}\%$ ለ. 3.25%   ሐ. 32.5%   መ. 325%

________14. $\frac{3}{8} = \frac{ሀ}{32}$ ከሆነ የ “ሀ” ዋጋ ስንት ነው?

ሀ. 12   ለ. 24   ሐ. 16   መ. 3

________15. ከታች ከተሰጡት ክፍልፋዮች ውስጥ ወደ አስርዮሽ ሲለወጥ አክታሚ አስርዮሽ የሚሆነውን ምረጡ።

ሀ. $\frac{19}{15}$ ለ. $\frac{1}{3}$ ሐ. $\frac{3}{4}$ መ. $\frac{2}{3}$

________16. $12^{\frac{1}{4}}\%$ በአስርዮሽ ሲገለፅ የትኛው ይሆናል?

ሀ. 12.25   ለ. 1.225   ሐ.0.1225   መ.0.01225

________17. $\frac{8}{9}$ ____________ $\frac{11}{10}$ በባዶ ቦታ ላይ የሚገባው ማወዳደሪያ ምልክት የትኛው ነው?

ሀ. ¿   ለ. ¿   ሐ.¿   መ. ≥

________18. አንድ ኩባያ ደረቅ የዉሻ ምግብ $1\frac{4}{5}$ ግራም ይከብዳል።

ዉሻዉ በቀን $6\frac{1}{3}$ ኩባያ ምግብ ቢመገብ በቀን ምን ያህል ግራም ምግብ ይመገባል?

ሀ. $\frac{57}{5}$ ግራም   ለ.$\frac{9}{5}$ ግራም   ሐ.$\frac{19}{5}$ ግራም   መ.$\frac{11}{5}$ ግራም

________19. አንድ ነጋዴ $2\frac{1}{2}$ ሜ ርዝመት ያለዉ ጥቅል ጨርቅ ገዛ።ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ብዛት 10 ጥቅል ጨርቅ ቢገዛ አጠቃላይ ስንት ሜትር ገዛ?

ሀ. 20.5 ሜ   ለ. 25 ሜ   ሐ. 250 ሜ   መ.2.5 ሜ

________20. የ 88 ትንሹ ብዜት ከሚከተሉት የቱ ነዉ?

ሀ. 1   ለ. 8   ሐ. 88   መ. 176

________21. የ 90 አካፋይ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ.12   ለ. 15   ሐ. 45   መ.30

________22. ለ $\frac{7}{9}$ አቻ ክፍልደፋይ የሆነዉን ምረጡ።

ሀ. $\frac{49}{65}$ ለ. $\frac{35}{65}$ ሐ. $\frac{42}{54}$ መ. $\frac{70}{900}$

_________23. የከበደ ቁመት ርዝመት $1\frac{3}{4}$ ሜትር ነዉ።የአበበ ቁመት ርዝመት 1.65 ነዉ።የሁለቱ ቁመት ድምር ስንት ይሆናል?

ሀ. 2.4 ሜ   ለ. 2.10 ሜ   ሐ. 1.4 ሜ   መ. 3.4 ሜ

_________24. የሁለት ሙሉ ቁጥሮች ት.ጋ.አ 1 ቢሆን ሁለቱ ሙሉ ቁጥሮች ምን ይባላሉ?

ሀ. ብቸኛ ሙሉ ቁጥር   ለ. ተተንታኝ ሙሉ ቁትር

ሐ. አንፃራ ብቸኛ ሙሉ ቁጥር   መ. ተጋማሽ ሙሉ ቁጥር

________25. “24 መ 5” ባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁትር ቢሆን እና ሙሉ ቁጥሩ ለ 3 ተካፋይ ለመሆን የ“መ” ቦታ ከሚከተሉት የትኛዉን ቁትር መተካት አለበት?

ሀ.1 ለ. 6 ሐ. 100 መ. 9

________26. $\frac{1}{10} \div 0.001 =$……………

ሀ.50 ለ.10 ሐ.100 መ.500

________27. 90000000 በአስር ርቢ ሲገለፅ

ሀ.9×10^9 ለ.9×10^8 ሐ.9×10^6 መ.9×10^7

________28. የ 48፣72 እና 80 ት·ጋ·ብ ስንት ነዉ

ሀ.360 ለ.720 ሐ.480 መ.960

________29. ከሚከተሉት ዉስጥ ትክክል ያልሆነዉን ምረጡ

ሀ. $33\frac{1}{3}\% = \frac{1}{3}$ ለ. $11\frac{1}{9}\% = \frac{1}{9}$ ሐ. $6.5\% = \frac{13}{200}$ መ. $62\% = \frac{31}{20}$

________30. $6\frac{1}{4} \div \frac{3}{2} =$………………

ሀ. $\frac{12}{50}$ ለ.$\frac{25}{6}$ ሐ.$\frac{25}{4}$. መ.$\frac{75}{8}$

የሂሳብ መልስ

1 ሐ 11 ለ 21 ሀ

2. ሀ 12 ለ 22. ሐ

3. ለ 13. መ 23.መ

4. ለ 14. ሀ 24. ሐ

5. መ 15. ሐ 25. ሀ

6. ሐ 16. ሐ 26. መ

7. ለ 17. ሀ 27. መ

8. ሐ 18. ሀ 28. ለ

9. ሐ 19. ለ 29. መ

10. መ 20. ሐ 30. ለ